

# ለአገር የመቆም ጥሪ!

*እኛ ከዚህ በታች ስማችን የተጠቀሰው በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአውስትራሊያና በአፍሪካ የምንገኝ ኢትዮጵያዉያን ዳያስፖራ ምሁራን በአሁኑ ወቅት አገራችን ከምትገኝበት የሰላምና የደህንነት፣ እንዲሁም ጂኦ-ፖለቲካዊ አደጋዎች በመነሳት የሚከተለዉን ለአገር የመቆም ጥሪ በትኅትና ልናስተላልፍ እንወዳለን።*

ዉድ የትዉልድ አገራችን በረዥም እድሜዋ ብዙ ጊዜ ታማ ድናለች። አንዳንድ ገዥዎቿ በድለዋታል፤ ሌሎች ተሠይፈዉላታል። ሁሉም በየተራ አልፈዋል። ልጆችዋ አልፎ አልፎ ተጣልተዋል፤ ተዋግተዋልም፤ ግን በጠባቸው መካከል እንኳን ለአገራቸው ተባብረዋል እንጅ፣ ምን ጊዜም ሕልዉናዋን ለጠላት አሳልፈው ሰጥተዉ አያዉቁም። የውጭ ጠላቶች በተለያየ ጊዜ ሊደፍሯት ሞክረዋል፤ ግን ሁሉም አፍረዉ ተመልሰዋል። በዚህም ጥንካሬዋ ለሌሎች የነፃነት ምሳሌ ሆና ኖራለች። ስለዚህም፣ ኢትዮጵያ በነፃነትዋ ቆማ፣ በኩራት ከትዉልድ ወደትዉልድ ተላልፋለች ። የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ልብ የገነባው ማንነታችንም ይህ የነጻነት ኩራት ነው!

በአሁኑ ጊዜ ያለው ተቀዳሚ ቅራኔ ኢትዮጵያ ትፍረስ! በሚሉና አትፈርስም! በሚሉ መካከል ያለ ፍልምያ ነው። አደገኛ የውስጥ ግጭትና የዉጭ ከበባና ዛቻ ባለበት በዚህ የታሪክ ወቅት፣ ልዩነቶቻችን ላይ እያተኮርን የምንበታተንበት ጊዜ ሳይሆን፣ የተነሳብንን አደጋ፣ በጥልቀትና አርቆ በማሰብ መርምረን፣ በምን መልክ እንመክታለን በሚለው ላይ ተቻችለን መተባበር ነው። የዉስጥ ቅራኔዎቻችን በተመለከተ፣ ትልቁን የሕልዉና አደጋ ካሸነፍን በኋላ እንደርስባቸዋለን ብለን እናምናለን። ይሄንን ቅደም ተከተል መገንዘባችን አገራችንን ከብዙ ፈተና ይታደጋታል ብለንም እናምናለን። በዘመናት የተፈጸሙ የአፍርሶ መገንባት ስህተቶችን መድገም የታሪክ ተወቃሽ ያደርገናል፡፡ ራዕይ፣ የፖሊሲ አማራጮች፣ እቅድና ልማት ሊታሰብና ሊተገበር የሚችለው፣ ቀጣይነቷ አስተማማኝ የሆነች ኢትዮጵያ ስትኖር ብቻ ነዉ። የፈረሰች ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ የምታበረክተዉ ነገር ቢኖር ተዛማች ፍልሰት፣ ስደት፣ ጦርነት፣ አለመረጋጋት፣ ነዉጥና ቀጠናዊ ዉድቀትን ብቻ ነው፡፡ የአገርን ደህንነት ባላስቀደሙ ህዝቦች ላይ የደረሰዉን ዉርደትና ዕልቂት በየአገሩ እየታዘብን ነው።

ኢትዮጵያን የመበታተን አደጋ ከጋረጡብን ዉስጥ፣ የዘር ፖለቲካን የሚያራምዱ ጽንፈኞች ዋነኞቹ ናቸዉ፡፡ አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉ መንግሥት የተረከባት አገር በኢኮኖሚ የከሰረች፣ በዕዳ የተዘፈቀች፣ በዘር የተከፋፈለች የጥቂት ግፈኞችና የግብረ-አበሮቻቸው መፈንጫ የነበረችን አገር ነው። ባለፉት ሶስት አመታት አገራችንን ወደተሻለ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ደረጃ ለማሸጋገር ጥረቶች ተደርገዋል። ተግዳሮቱ ግን የዚያኑ ያህል በርትቷል።

ዘረኛ ጽንፈኞች፣ ኢትዮጵያዊ ወገናቸዉን እያሳደዱ መግደላቸውን በደስታ የሚደግፉ የዉጭ ጠላቶችም አሉ። በእጅ አዙርም ጽንፈኞችን እየደገፉ እርስ በእርስ እንድንባላ ያደርጋሉ። እነሱም የአገራችንን መበታተን አድፍጠው ይጠብቃሉ። ለአገር ውስጥ መከፋፈላችንም ሆነ ለዉጭ ጠላት ክፍተት መፈጠር ዋነኛው ተጠያቂ፣ የአሁኑ መንግሥት የወረሰውና ሊያቃናው ያልሞከረው የዘር ፖለቲካ ተቋማዊ መዋቅር እንደሆነ እንረዳለን። ብሎም እስካሁን ለተደረገው የወገን ዕልቂት መንግሥትን ከተጠያቂነት አያድነውም። በአገራችን በግፍ ንፁሃን ወገኖቻችንን እንዲገደሉ፣ እንዲፈናቀሉ፣ እና ጉዳት እንዲደርስባቸው ያደረጉ አካላት ለፍትህ እንደሚቀርቡ እንጠብቃለን። የአገርን ሰላምና የዉስጥ አንድነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ፣ ይህንን በብዙ ዓመታት ሴራ የተዘረጋ የዘር መዋቅራዊ ችግር መፍታትም የግድ ነዉ። ነገር ግን ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ረዥም ጊዜ የሚወስድ ሂደት መሆኑንም ደግሞ መረዳት ይገባል።

አሁን እንደ አገር ያጋጠሙን ችግሮች ገዝፈው ቢታዩም፣ በሰከነ መንገድ ከተነጋገርን፣ ከተዛዘንን እና ለኢትዮጵያ ቅድምያ ከሰጠን በድል እናልፋቸዋለን። በጋራም አገራችንን አሳድገን ለተተኪ ትዉልድ እናስረክባለን። ለሺህ አመታት ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መንግሥታትና ሥርዓቶች አልፈዋል፤ ኢትዮጵያ ግን አለች። ነገም ትቀጥላለች።

አሁን በቆምንበት ወቅት፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የራሳችንን ገመና ለጠላት አሳልፈን ከሰጠንና ወደእርስ በእርስ ጦርነት ከገባን፣ እጅግ ከባድ አደጋ ሊከሰት ይችላል። ጠላቶቻችንም የሚዶልቱት እዚህ አዘቅት ዉስጥ እንድንገባ ነው። አደጋው በሰዉ ሞት ብቻ የሚያቆም ሳይሆን፣ መመለሻ የሌለው የአገር መበተንን ያስከትላል፡፡ ኩራታችንም፣ ነፃነታችንም አብሮ ይከስማል። በአሁኑ ሰዓት፣ የዉጭን ጠላት ለመቋቋም የሚያስችለን ብቸኛና አማራጭ የሌለዉ ኃይል፣ ከነድክመቱም ቢሆን፣ በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው መንግሥት ነዉ። በመንግሥት ላይ አግባብ ያለዉ ወቀሳና ተቃዉሞ ማድረግ ተገቢ ነው። አላማዉ ግን መንግሥት ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲሰጥና አገራችንን እንዲታደግ እንጂ፣ መንግሥትን ለማፍረስ በጭራሽ መሆን የለበትም። አገራችን ጨርሳ የምትፈርስበትን ሥራ እየሰሩ የመፍትሔ አካል መሆን አይቻልም።

**የአገር አድን ጥሪ!**

ከላይ ባጭሩ እንዳመላከትነዉ አሁን አገራችን የዉስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከዉጭም ከፍተኛ ጂዖ-ፖሊቲካዊ ስጋቶች ከፊቷ ተደቅነዉባታል። ጠላቶቿ መፍረሷን ለማዬት አሰፍስፈዉ እየጠበቁ ቢሆንም፣ ይህንን ተግዳሮት በአሸናፊነት በመወጣት ልታስመዘግባቸው የምትችላቸው አያሌ ዕድሎችም ከፊቷ እንዳሉ እንረዳለን። ስለሆነም ለመላዉ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዉያን የሚከተሉትን ጥሪዎች እናቀርባለን።

፩ኛ-አገራዊ ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ ሳይራዘም በሰላምና በተአማኒነት እንዲጠናቀቅ በአፅንዖት እያሳሰብን፣ በዉጤቱ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያጠናክር ጉዞ እንደምንጀምር ከፍተኛ ተስፋ በማድረግ ነው።

፪ኛ-መንግሥት የሰላም ማስከበር ሃላፊነቱን በበለጠ ቁርጠኝነት ተነስቶ፣ ሳያወላዉል፣ ወንጀለኞችን ለፍርድ እንዲያቀርብና ጭፍጨፋዎችን እንዲያስቆም፤ በተጨማሪም ሐዘን ለበዛበት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው የማረጋጋት ተግባርን በበቂ እንዲያከናውን እናሳስባለን።

፫ኛ-የኅዳሴ ግድብ ፍጻሜን ለማደናቀፍ የሚጣጣሩ ጠላቶቻችንን ከመቼዉም በበለጠ ተባብረን እንድንቋቋም ለኢትዮጵያን ወገኖቻችን ጥሪ እናቀርባለን።

፬ኛ-አገር-አፍራሽ ተልዕኳቸዉ ገሃድ የወጣ ጽንፈኞችን ወደ ስልጣን ለመመለስ ምርጫዉን በሽምግልና ሰበብ እያንጓተቱ ለማስተጓጎልም ሆነ ማናቸዉንም በዉጭም ሆነ በዉስጥ የአገራችንን ገፅታ ለማጠልሸት የሚደረጉ ድብቅና ገሃድ የሴራ እንቅስቃሴዎችን እንቃወማለን።

፭ኛ-ኢትዮጵያን መንግሥት-አልባ ለማድረግ የሚደረገዉን ጂዖ-ፖሊቲካል የከበባ ደቦ በመመርመር ሴራውን እያጋለጥን፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ያሰማሯቸውን የውስጥና የውጭ ቅጥረኞች በየመስኩ እንድንመክት ከፍተኛ አገራዊ ጥሪ እናቀርባለን።

፮ኛ-የአገራችን ኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ የፖለቲካ ነፃነትና የግዛት አንድነት በፍጹም ለድርድር አይቀርብም። ይህንን ገሃድ ሃቅ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት በቅርቡ ባወጣው መግለጫ በአፅንዖት ሲያስረግጥ፣ ሌሎችም ይህንን ጽኑ አቋማችንን እንዲገነዘቡት በጥብቅ እናሳስባለን።

፯ኛ-ባለፉት ዓመታትና በተለይም ባለፉት ጥቂት ወራት፤ የበርካታ ንጹሃን ሕይወት በግፍ የተቀጠፈባቸው የጭካኔ አድራጎቶች በግልጽ የሚያረጋገጡት፣ አገራችን እና ህዝባችን የተደቀነባቸውን አደጋ ጥልቀትና እና የዚህችን ሰዓት ወሳኝነት ነው። በመሆኑም ሁሉንም በማስተዋል ልናደርጋቸው የሚገቡንንም ሆነ መቆጠብ ያሉብንን ነገሮች ከነምክንያቶቻቸው በውል ተረድተን አሁኑኑ መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ነገ ያለጥርጥር ይረፍድብናልና!

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**

- Dr. Abebech Demissie, Ottawa, Canada
- Dr. Abera Molla, Denver, USA
- Dr. Abraham Betre, M.D., California, USA
- Dr. Amir Ibrahim, M.D., Toronto, Canada
- Dr. Awgechew Teshome, Ottawa, Canada
- Awlae Woldehanna, RN, Saskachewan, Canada
- Dr. Benyam Gessesse, M.D., Philadelphia, USA
- Professor Emeritus Berhanu Mengistu, USA
- Dr. Bizu Gelaye, M.D., Boston, USA

- Professor Damtew Teferra, South Africa
- Prof. Demel T. Fanta, Botswana
- Dr. Desalegne Bayih, M.D., Sweden
- Professor Enawgaw Mehari, M.D., Nashville, USA
- Dr. Efrem Alemayehu, M.D., Toronto, Canada
- Engineer Elleni Mengesha, Sweden
- Dr. Endale Ketefo, Sweden
- Dr. Fantahun Degneh, Germany
- Dr. Fassil Tefera, M.D., New York, USA
- Dr. Fikre Germa, M.D., Toronto, Canada
- Dr. Fisseha Solomon, Winnipeg, Canada
- Dr. Fitsum Tariku, British Columbia, Canada
- Dr. Gebeyehu Teferi, M.D., Washington D.C., USA
- Dr. Gebrehiwot Lebsekal, Vancouver, Canada
- Dr. Getachew Felleke, M.D., New York, USA
- Dr. Getnet Asrat, M.D., Ottawa, Canada
- Dr. Getu Biftu, Calgary, Canada
- Dr. Girma Lulu, Calgary, Canada
- Dr. Girma Molla, Australia
- Dr. Girma Aman, Kitchner, Canada
- Dr. Guadie Sharew, Eswatini
- Professor Kassa Darge, Pennsylvania, USA
- Assoc. Professor Kebede Begna, M.D., USA
- Mr. Kidanemariam Jembere, South Africa
- Professor Makeda Semret, Montreal, Canada
- Professor Mammo Muchie, South Africa
- Dr. Mekonen Bayissie, USA
- Dr. Melaku Game, M.D., Canada
- Dr. Mengistu Yemane, M.D., Tennesse, USA
- Dr. Mesfin Seifu, M.D., Ohio, USA
- Professor Messay Kebede, Ohio, USA
- Dr. Moges Sisay, M.D., Indiana, USA
- Prof. Mulatu Fekadu, South Africa
- Dr. Mulu Geletu, Toronto, Canada

- Prof. Mulugeta F. Dinbabo, South Africa
- Professor Nega Debela, Ohio, USA
- Engineer Samson Engeda, San Diego, California
- Dr. Samuel Tenaw, South Africa
- Professor Seid Hassen, USA
- Dr. Shiferaw Adilu, Alberta, Canada
- Professor Solomon Aklilu, Ottawa, Canada
- Dr. Solomon Basore, Calgary, Canada
- Professor Sissay Asefa, Michigan, USA
- Professor Solomon Harrar, Kentucky, USA
- Dr. Solomon Kibret, USA
- Mr. Solomon Teffera, USA
- Dr. Tadesse Desta, M.D., California, USA
- Dr. Tariku Teshale, M.D., Sweden
- Dr. Tesfalem Tegegn, South Africa
- Dr. Tihut Asfaw, Ottawa, Canada
- Professor Tilahun Adera, Virginia, USA
- Dr. Wondimu Mekonnen, UK
- Dr. Wondwossen Gebre, M.D., New York, USA
- Professor Wondwossen Gebreyes, Ohio, USA
- Professor Worku Abera, Montreal, Canada
- Engineer Yeshitila Mulugeta, San Diego, USA
- Professor Yohanes Tiruneh, San Diego, USA
- Dr. Yonas Biru, Washington D.C., USA
- Professor Yonas Geda, Arizona, USA
- Dr. Zergabachew Asfaw, New York, USA
- Dr. Zewdu Lisanu, M.D., Kentucky, USA

**Contacts:**


- Africa: Professor Damtew Teferra | datemek@yahoo.com |
- Canada: Dr. Tihut Asfaw | tihut_asfaw@yahoo.ca |
- Europe: Dr. Tariku Teshale | taridoc@yahoo.com |
- USA: Professor Enawgaw Mehari | em_mehari@yahoo.com |